## አንድ ቅንጅት፣ አንድ ድምፅ - የቅንጅት ዓለም አቀፍ ካውንስል ሚና

### ከቅንጅት ዓለም አቀፍ ካውንስል የተሰጠ መግለጫ
### ነሐሴ 26 ቀን 1999 ዓ.ም
Spetember 1, 2007

ዓለም አቀፉ ለሰብዓዊ መብትና ለእስረኞች ጥብቅና የቆመው ድርጅት (አምነስቲ ኢንተርናሽናል) "የሕሊና እስረኞች" ያላቸውን የቅንጅት መሪዎች በሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም ከኢፍትሐዊ እስራት ነፃ መሆን በታላቅ ናፍቆትና ደስታ አክብረናል። እነዚህ ከሕግ ውጭ ታስረው የነበሩ የሕዝብን ፍቅር የተጎናጸፉ መሪዎች እንደተፈቱ ወዲያውኑ በፖለቲካውና በዲፕሎማሲው መስክ አከታትለው በአንድነት የወሰዷቸው እርምጃዎች፣ በአገር ቤት ብቻ ሳይሆን፣ በስደቱ ዓለም የምንኖረውን ኢትዮጵያውያን ጭምር በቅንጅት ላይ ያለንን ታላቅ ዕምነትና ተስፋ ይበልጥ አጠናክሮታል። ይህ ውሑድና ጠንካራ ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰላም፣ ለብሔራዊ እርቅ፣ ለነፃነት፣ መላውን ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ለሚያሳትፍ ዲሞክራሲ፣ ከጎረቤት አገሮች ጋር በሰላም ለመኖርና ለፈጣን ማህበራዊና የኢኮኖሚ እድገት ያለውን ፍላጎትና ተስፋ የሚያንፀባርቅና የሚወክል መሆኑ ከምን ጊዜውም በበለጠ ሁኔታ ተረጋግጧል። የአሁኑና ተከታታዩ የኢትዮጵያ ትውልድ ከፍርሃት፣ ከመከፋፈል፣ ከብቸኛነት፣ ከጭቆና፣ እርስ በእርስ ከመወነጃጀልና ከመጠራጠር፣ በጠቅላላውም መጠን ከሌለው የድህነትና የስቃይ አዘቅት ወጥተው በሰላም፣ በፍቅርና በመተሳሰብ ሁሉም በልጽገው እንዲኖሩ ለማድረግ የቅንጅት ራዕይ፣ መሰረታዊ ዓላማና የሥራ እቅድ ነው።

በቅንጅት አመራር ስር ዓለም አቀፍ ካውንስል የተፈጠረው ለቅንጅት ፓርቲና አመራር በተቀነባበረና ወቅታዊ በሆነ መልክ የማቴሪያል፣ የገንዘብ፣ የሃሳብ፣ የሕዝብ ግንኙነትና የዲፕሎማሲ እርዳታና ድጋፍ ለመስጠት ነው። በግንቦቱ ምርጫ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ከዳር እስከ ዳር ያነቃቃውና ያሰባሰበው የቅንጅት መንፈስ ተጠናክሮ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት አማራጭ የሌለው መንገድ የቅንጅት አንድነት መጽናትና በአንድ ድምጽ መናገር ነው። ይህ ዓለም አቀፍ ካውንስልም ኃላፊነቱን የሚወጣው ከዚሁ አንድ ወጥ ከሆነው የቅንጅት አመራር በሚሰጠው ውሳኔና አደራ መሰረት ነው።

ካውንስሉ የተመሰረተበት ብቸኛ መመሪያ የቅንጅትን ራዕይ፣ ዓላማና የሥራ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ወቅታዊ እርዳታና አገልግሎት ለመስጠት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። ቅንጅት ሙሉ የሕዝብ አመኔታ አግኝቶ የታወቀበትና ተወዳጅነት ያተረፈበት ዓይነተኛ ምክንያት በሕዝብ የበላይነት ላይ በተመሰረተ የዲሞክራሲ አመራር መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥፋት ወደ ደኅንነትና ወደ እድገት ለመሸጋገር የሚያደርገው ቆራጥ የሆነ ሰላማዊ ትግል ነው። በእኛ አስተያየት፣ በውጭው ዓለም በቅንጅት ደጋፊዎች ውስጥ ከተከሰተው ጀምሮ፣ በተቃዋሚ ጎራዎች መካከል የሚኖረው ማንኛውም አለመግባባት በግለ ሰብ ላይ የሚያነጣጥር መሆን የለበትም፤ ሊሆንም አይገባም። ልዩነቶች ቢኖሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአጭር፣ የረጅምና የዘለቄታ ፍላጎትና ደኅንነት በሚጠበቅበትና በሚጎለምስበት መስፈርት ሊመዘኑ፤ እንዲሁም በቅን መንፈስ ተመርምረውና ውይይት ተደርጎባቸው ውሳኔ ሊያገኙ ይገባል።

ቅንጅትና ሀቀኛ መሪዎቹ የተሰቃዩበትና አሁንም በመሰቃየት ላይ ያሉት ለግል ፍላጎት፣ ሥልጣንና ዝና ተብሎ አይደለም። መስዋዕት የከፈሉትና የሚከፍሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ነፃነቱንና የዲሞክራሲ መብቱን በወቅቱ እንዲጎናጸፍ ለማድረግ ነው። ቅንጅት የኢትዮጵያን ማኅበረ ሰብ ኑሮ ለማሻሻል የተጣለበት ተስፋ ለሕዝቡ ካለው ታማኝነትና ለመክፈል ከተዘጋጀው መሥዋዕትነት ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

ስለዚህ የዓለም አቀፉ ካውንስል ተግባር ቅንጅትና ታማኝ መሪዎቹ የድርጅቱ ራዕይ፣ ተልእኮና ዓላማ ግባቸውን እንዲመቱ ለሚያደርጉት ከፍ ያለ ጥረት እርዳታ ማቅረብ መሆኑን አበክረን እንገልጻለን። ይህንንም ቅን አስተዋጽኦ ለማድረግ ስንጣጣር፣ አንዳንድ ለራሳቸው ተራ ጥቅም፣ ዝና፣ ሀብትና የፖለቲካ ሥልጣን ሲሉ የተሰለፉ ግለሰቦችና የውጭ ኃይሎች እርስ በእርስ የሚከፋፍልና የሚያደናቅፍ የተንኮል መረባቸውን ሊጥሉብን እንደሚችሉ ጠንቅቀን ማወቅና መከላከል ይኖርብናል። ይህን የመሳሰለው አደገኛ ዘመቻ የቅንጅትን ሕዝባዊ ኃይል ለመሸርሸርና ለማዳከም፣ ብሎም ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ሆኖ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አሁን ካለበት አሰቃቂ ሁኔታ ተረባርቦ በማውጣት ነፃነት፣ ዲሞክራሲና ብልጽግና ለማጎናጸፍ ያለውን ተስፋ የሚያጨናግፍ ሙከራ ለማድረግ ነው። ይህን የተደቀነብንን አደጋ ሁላችንም በትጋትና በኅብረት ልንቋቋመውና ልንገታው ያስፈልጋል።

የቅንጅት መሪዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም፣ ብሔራዊ እርቅ፣ ነፃነት፣ ክብር፣ አንድነት፣ ዲሞክራሲ፣ በጠቅላላውም የኑሮ መሻሻል ሲሉ የከፈሉት አቻ የሌለው መሥዋዕትነትና ለሕዝቡ ያተረፉት ተመክሮ ለዘለዓለም ሲታወስ ይኖራል። ከዚህ ታላቅ መሥዋዕትነት ከተከፈለበት የቅንጅት ራዕይና ግብ ዓለም አቀፉ ካውንስል አንዲት ቅንጣት እንኳ ዝንፍ ሳይል ለግል ጥቅማቸው የሚወራጩትንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ስቃይ ለማራዘም የሚጥሩትን፣ እንዲሁም አውቀውም ሆነ በመደለል በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት የጭቆና ዘመን ለማራዘም ምክንያት የሆኑትን ሁሉ ያለአንዳች መዘናጋት ይቋቋማቸዋል። የራሳቸውን ጥቅማጥቅም በማስቀደምና በማሳደድ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ደኅንነት፣ ነፃነትና የተሟላ ሰላማዊ ኑሮ ለመርገጥ የሞከሩና የሚሞክሩ ሁሉ ውሎ አድሮ ሕዝቡና ታሪክ ምንኛ እንደሚፈርዱባቸው ጊዜው ሳይመሽ አሁኑኑ ካለፈው ጭምር በመማር ሊታረሙና ቀናውን መንገድ ሊይዙ ይገባል።

በግል ጥቅም፣ በክፋትና በማን አለብኝነት ተነሳስተው በጥፋት ዘመቻ የተሰማሩትን ግለሰቦችና ድርጅቶች አፍራሽ ተግባር ለማክሸፍ በመላው ዓለም የሚገኘው፣ የቅንጅት ደጋፊና ተባባሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ ዲያስፖራ ሁሉ በትጋት እንዲሰለፍ አደራ በማለት ጥሪያችንን እናቀርባለን። አንድ ቅንጅት አንድ ድምፅ ዓርማችን ነው፤ ወደፊትም በዚሁ እንጸናለን። ይህም ለአሁኑና ለተተኪው ትውልድ ሁሉ አማራጭ የሌለው ወደ ዘላቂ ለውጥና ሁለገብ እድገት መሸጋገሪያ ድልድይ ነው።

የቅንጅት ዓለም ቀፍ ካውንስል
ነሐሴ፤ 1999 ዓ.ም